# መመሪያ ቁጥር 22/2007 ዓ/ም

## መደበኛ ነዋሪነታቸው በውጭ አገር የሆነና በአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ውስጥ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ኢትዩጲያውያንና የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ-ኢትዩጲያዊያን የሚመዘገቡበትንና የሚስተናገዱበትን የአሰራር ስርዓት ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መመሪያ

የኢፌዴሪ መንግስት በተለያዩ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በትውልድ አገራቸው ሁሉን አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የዲያስፖራ ፖሊሲ ቀርፆ ከታህሣሥ ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ በመሆኑ፤

በሰነዱ ክፍል ሁለት ቁጥር /5/ ንዑስ ቁጥሮች /1/ እና /4/ ስር እንደሰፈረው ከዚሁ ፖሊሲ ግንባር ቀደም ግቦች መካከል “በውጭ የሚኖሩ ኢትዩጲያውያንን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ” እና “የውጭ ምንዛሪ ማስገቢያ መንገዶችንና የዲያስፖራውን ተሳትፎ ማሳደግ” የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሆነው በመገኘታቸው፤

ዲያስፖራው በግልና በማህበር ተደራጅቶ በክልሉ ከተሞች ውስጥ ቁጠባን መሠረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት መገንቢያ ቦታ ስለሚያገኝበት ሁኔታ በጥናት ላይ የተመሠረተ የአሠራር ስርዓት እንደሚዘረጋ በሀገሪቱ የቤት አቅርቦት ስትራቴጅ ማዕቀፍ ውስጥ ጭምር የተካተተ በመሆኑ፤

ከዚሁ በመነሳት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በግል በመመዝገብም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት በክልሉ የቤት ልማት ፕሮግራም ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እነዚሁ ወገኖች ገንዘባቸውን በውጭ ምንዛሪ ቆጥበው በተጠቀሰው ፕሮግራም ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የቤት ባለቤት እንዲሆኑና ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ከማጠናከር ጎን ለጎን ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን የምዝገባ፣ የአደረጃጀትና የቁጠባ አሰራሩን በግልፅ የሚያሳይ ቀልጣፋ የአፈፃፀም ስርዓት መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ /58/ ንኡስ አንቀጽ /7/ እና በብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም አንቀፅ /36/ ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ነዋሪነታቸው በውጭ አገር የሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የሚመዘገቡበትንና የሚስተናገዱበትን ስርዓት ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ም/ቤት መመሪያ ቁጥር 22/2007 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የኢትዮጵያ ዲያስፖራ"** ማለት ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም የሌላ አገር ዜግነት ያለው ትውልደ-ኢትዮጵያዊ ነው፤
2) **"ተመላሽ ዲያስፖራ"** ማለት ኑሯቸውን በውጭ አድርገው ከቆዩ በኃላ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አገር ቤት ከተመለሱ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸውና በተለያዩ የስራ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን የሚገልፅ ሀረግ ነው፤
3) **"ሀዋላ"** ማለት በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ወይም ሌሎች የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካኝነት ገንዘብ የሚዘዋወርበት ዘዴ ነው፤
4) **"ዲፕሎማቲክ ፓውች"** ማለት በቪየና ኮንቬንሽን መሰረት ለአንድ ሚሲዮን ኦፊሴላዊ ሥራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሠነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ነው፤
5) **"ሚሲዮን"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ አገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ነው፤
6) **"የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር"** ማለት በኢትዩጲያ ውስጥ መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች ተፈላጊውን የከተማ ቦታ አግኝተው ይህንኑ ለመገንባት በጋራ ተሰባስበው የሚያቋቁሙትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ነው፤

7) **"ነባር የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር"** ማለት በውጭ አገር በሚኖሩ ኢ.ትዮጵያዊያንና ትውልደ-ኢ.ትዮጵያዊያውያን እንዲሁም በተመላሽ ዲያስፖራዎች አማካኝነት ተደራጅቶ አግባብ ካለው የማህበራት ማደራጃ ተቋም የምዝገባ ሠርተፊኬት የወሰደ፣ ገንዘብ በዝግ የባንክ ሂሣብ ያስቀመጠና ይህ መመሪያ እስከፀናበት ቀን ድረስ ለግንባታ የጠየቀውን የከተማ ቦታ ያልተረከበ ማናቸውም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ነው፤

8) **"አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር"** ማለት ይህ መመሪያ በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በክልሉ ከተሞች ውስጥ ታውን ሃውስና አፓርትመንት ቤቶችን ለመገንባት በሚፈልጉ የውጭ አገር ነዋሪ ኢ.ትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢ.ትዮጵያውያን አባልነት እንደ አዲስ የሚቋቋምና የሚመዘገብ የቤት ህብረት ስራ ማህበር ነው፤

9) **"የግል ተመዝጋቢ"** ማለት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢ.ትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢ.ትዮጵያዊያን አፓርትመንት ወይም ታውን ሃውስ ለመገንባት ይቻላቸው ዘንድ በተናጠል ወይም በነፍስ-ወከፍ ከተመዘገቡ በኃላ በጋራ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሥርዓት ነው፤

10) **"የውክልና ስልጣን ማስረጃ"** ማለት በህግ የተደነገገን ሥርዓት ተከትሎ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ በህግ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ እና እንደተገቢነቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ሆነ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ማናቸውም የውክልና ስልጣን መግለጫ ሰነድ ነው፤

11) **"ባንክ"** ማለት የኢ.ትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው፤

12) **"የቤቶች ልማት ኤጀንሲ ወይም ድርጅት"** ማለት በግል ተመዝግበውም ሆነ በማህበር ተደራጅተው መኖሪያ ቤታቸውን ይገነባላቸው ዘንድ መንግስትን ለሚጠይቁ አካላት በሚኖራቸው ውል መሰረት የቤት ግንባታ ለማካሄድና ለማስረከብ በክልሉ መንግስት የተቋቋመና ለዚሁ ተግባር ፈቃድ የተሰጠው ማናቸውም ድርጅት ነው፤

13) **"ዲፕሎማት"** ማለት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሌሎች መንግታስዊ መሥሪያ ቤቶች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሚሲዮኖች በኩል በውጭ ግንኙነት ዘርፍ ተመድቦ የሚያገለግልና በዜግነት ኢ.ትዮጵያዊ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ ነው፤

14) **"ሎካል ሠራተኛ"** ማለት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በሌሎች መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሚሲዮኖች ተቀጥሮና ተመድቦ በማገልገል ላይ የሚገኝ ኢ.ትዮጵያዊ ነው፤

15) **“አደራጅ አካል”** ማለት  በክልሉ ውስጥ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን ለማደራጀትና ለመመዝገብ በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሲሆን  የተዋረድ አካላቱን ይጨምራል፤

16) **“ታውን ሀውስ”** ማለት የጂ+1 ወይም የጂ+2 ደረጃ ያለው ህንፃ ሆኖ ራሱን የቻለ ወለል፣ መጠነኛ ግቢና መግቢያ ያለው ከአጐራባች ህንፃዎች ጋር በግድግዳ የተያያዘ መኖሪያ ቤት  ነው፤

17) **“አፓርትመንት”** ማለት ጂ+4 እና ከዚያ በላይ የሆነ ወለል ያላቸው እና በከተማው መሬት አጠቃቀም ፕላን መሠረት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ሕንፃዎች ሆነው በጋራ መኖሪያ ቤት ህግ መሠረት በግል ባለቤትነት የሚያዙ የተሟሉ መኖሪያ ቤቶችን ያመለክታል፤

18) "ሊዝ" ማለት በጊዜ በተገደበ ውል መሰረት በከተማ ቦታ የመጠቀም መብት የሚቋቋምበት  የመሬት ይዞታ ስሪት ነው፤

19) "የሊዝ መነሻ ዋጋ " ማለት ዋናዋና የመሰረተ ልማት  አውታሮችን ለመዘርጋትም ሆነ ነባር ግንባታዎች በሚገኙበት አካባቢ አነዚህኑ ግንባታዎችና ተያያዥ ንብረቶች ለማንሳት የሚያስፈልገውን ወጭ እንዲሁም ለተነሽዎች የሚከፈለውን ካሳና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ያስገባ የመሬት ሊዝ  ዋጋ ነው፤

20) "ዋና ዋና ከተሞች" ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛና መካከለኛ ከተሞችን ያጠቃልላል፤

21) **“ቢሮ”** ማለት የክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ነዉ፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከዚህ በፊት በመንግስት ድጋፍና አስተባባሪነት በአገሪቱ ውስጥ በሚካሄዱት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎች ያልሆኑትንና በግል ተመዝግበውም ሆነ  በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው በክልሉ ከተሞች ውስጥ አፓርትመንት ወይም ታውን ሃውስ የመገንባት ፍላጐት ያላቸውን በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣  ትውልደ-ኢትዮጵያውያንና ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት፣ እንዲሁም በተለያዩ  የኢፌዴሪ ሚሲዮኖች ተቀጥረው ወይም ተመድበው በሥራ ላይ የሚገኙትን ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች አስመልክቶ በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማዎች

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በክልሉ መንግስት የቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ለመሆን የሚያስችሏቸውን የምዝገባ መስፈርቶችና የመስተንግዶ ስርዓት ግልፅ ማድረግ፤
2) በምዝገባው ሂደትና አፈፃፀም የሚሳተፉት ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ስልት መዘርጋትና ሀላፊነታቸውን ማደላደል፡፡

## 5. መርሆዎች

ይህ መመሪያ በሚከተሉት መርሆች ላይ ተመስርቶ ይተገበራል፡-

1) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን መንግስት በዘረጋቸው የቤት ልማት ፕሮግራሞች በመሳተፍ ለክልሉ ብሎም ለአገሪቱ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ሁኔታዎች ይመቻቹላቸዋል፤
2) መረጃዎች ግልጽና ፈጣን የምዝገባ፣ የአደረጃጀትና የቁጠባ ስርዓትን በተከተለ መንገድ ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፤
3) ባለድርሻ አካላት በተቀናጀና አሳታፊ በሆነ አግባብ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን፣ ትውልደ-ኢትዮጵያውያንና ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን ለመደገፍ የክልሉ መንግስት የሚያደርገውን ጥረት እንዲያግዙ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# በግል ተመዝግበው ወይም በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው በቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊነት ስለሚያመለክቱ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዩጲያዊያንና ትውልደ-ኢትዩጲያውያን የመስተንግዶ አግባብ

## 6. በምዝገባ ወቅት መሟላት ስላለባቸው ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች

1) በግላቸው ወይም በማህበር ተደራጅተው በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ በታውን ሀውስ ወይም በአፓርትመንት አይነት መኖሪያ ቤት የመገንባት ፍላጎት ያላቸው የውጭ ሀገር ነዋሪ ኢትዩጲያውያንና ትውልደ-ኢትዩጲያውያን ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች በማሟላት ሊመዘገቡ ይችላሉ፡-
   ሀ) እድሜው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነና በህግ ወይም በፍርድ ያልተከለከለ፤

ለ) የጸና የፓስፖርትና ከሚኖርበት አገር የጸና የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ወረቀት የተረጋገጡ ቅጂዎችን ያቀረበ፤

ሐ) የሌላ አገር ዜግነት ያለው እንደሆነ የጸናና የተረጋገጠ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ወረቀት ቅጂ ያቀረበ፤

መ) ሁለት የፓስፖርት መጠን ያላቸው የራሱን ፎቶ ግራፎች ያያዘ ፤

ሠ) ባለትዳር በሚሆንበት ጊዜ የተረጋገጠ የህጋዊ ጋብቻ ምስክር ወረቀት ቅጅ ያቀረበ፤

ረ) ቀደም ሲል መንግስት በዘረጋቸው ሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራሞች አማካኝነት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያልሆነ ወይም ለመጠቀም ያልተመዘገበ ወይም ተመዝግቦም ከሆነ ምዝገባውን መሠረዙን ወይም መተውን ያሳወቀ፤

ሰ) በክልሉ ውስጥ በሚገኝ በየትኛውም የከተማ አካባቢ ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ ቦታ የሌለው ወይም ቀደም ሲል ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፤

ሸ) የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበሩ የወሰነውን የአባልነት መመዝገቢያ ክፍያና ሌሎች መዋጮዎችን ለመፈፀም የሚችል፤

ቀ) በአባልነት ለተመዘገበበት ማህበር እንዲሰጥ ከተወሰነው የከተማ ቦታ ላይ ለሚለቁት ተነሽ ባለይዞታዎች የሚከፈለውን ካሣ እንዲሁም ነባር ግንባታዎችና ንብረቶችን ከስፍራው ለማንሳትም ሆነ ለመሰረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ የሚያሥፈልጉትን ሌሎች ወጪዎች በቅድሚያ መክፈል የሚችል ፤

በ) አግባብ ባለው የክልሉ መንግስት አካል በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ፤

ተ) በመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ሙሉ ወጪ በውጭ ምንዛሪ ከፍሎ በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችል፤

ቸ) ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር “ተ” መሰረት ገቢ ከተደረገው ጠቅላላ የግንባታ ወጪ ውስጥ 50 ከመቶ የሚሆነውን በምዝገባ ወቅት በሚኖርበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በኩል ሂሳብ በመክፈት አስቀድሞ ያስቀመጠና በአባልነት የተመዘገበበት የመኖሪያ

ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለግንባታ የተዘጋጀውን የከተማ ቦታ በሚረከብበት ጊዜ ደግሞ ቀሪውን 50 ከመቶ አጠናቆ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ ፤

ኃ) የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማዎችና መርሆዎች ለማክበርና የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ፡፡

2) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ የተገኘ ማንኛውም የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጲያዊ ወይም ትውልደ-ኢትዮጲያዊ ለምዝገባው የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅና የዉል ሰነድ ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር ተቀብሎ መሙላትና ፈርሞ መመለስ ይኖርበታል፤

3) በተለያዩ ምክንያቶች በአካል ቀርበው ሊመዘገቡ የማይችሉ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁኔታዎች አሟልተው በተወካዩቻቸው አማካኝነት ሊመዘገቡ ይችላሉ፡-

ሀ) የወካዩ የጸና ፓስፖርትና ከሚኖርበት አገር የተሰጠ የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ አባልነት መታወቂያ ወረቀት የተረጋገጡ ቅጂዎች፤

ለ) ወካይም ሆነ ተወካይ ወይም ሁለቱም የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው እንደሆነ የወካዩ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ወረቀት የተረጋገጠ ቅጂ፤

ሐ) የፓስፖርት መጠን ያላቸው የወካዩ ሁለት ፎቶ ግራፎች፤

መ) በተመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት ከግንባታው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ 50 ከመቶ የሚሆነው በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ በወካዩ ስም በውጭ ምንዛሪ ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ የሚያሣይ ደረሰኝ የተረጋገጠ ቅጅ፤እና

ሠ) ተወካይ ወካዩን በተመለከተ የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ሆኖ ቢገኝ ወደፊት ተጠያቂ ለመሆን የተፃፈ የዝግጁነት መግለጫ፡፡

## 7. ስለማህበራት ምዝገባና ይኸው ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1) የትኛውም ማህበር በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበርነት መመዝገብ የሚችለው መላ የማህበሩ አባላት ከተገመተው ጠቅላላ የግንባታ ወጪ 50 ከመቶ የሚሆነውን በዝግ የባንክ ሂሣብ ማስገባትና ማስያዝ ሲችሉ ብቻ ይሆናል፤

2) ሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የየራሳቸው መጠሪያ ስም ይኖራቸዋል፡፡ በዚሁ ማህበር የታቀፉ አባላት የዚህ መመሪያ አባሪ ሆኖ የሚቀርብላቸውን ቅጽ /005/ በራሳቸው፣ ካልቻሉ ደግሞ በህጋዊ ወኪሎቻቸው አማካኝነት መሙላት ይገባቸዋል፤

3) በክልሉ ውስጥ የሚደራጁ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸውን የግንባታ ዲዛይን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ዲዛይኑ እንደ አግባቡ ስልጣን በተሰጠው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፤

4) የነባር ማህበራትን አመዘጋገብ በተመለከተ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጉዳዩን ከሚመለከተው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ የሥራ ክፍል ጋር በጋራ ተስማምተው ለክልሉ የዲያስፖራና ህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በሚያቀርቡት ዝርዝር ስምምነት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፤

5) በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚፈልጉ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ የዲያስፖራ አባላት የመረጡትን ከተማ ለይተው እንዲያሳውቁና አስፈላጊው ቅድመ-ዝግጅት ተሟልቶ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

## 8. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሚሲዮኖች ተመድበው ስለሚያገለግሉ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች ምዝገባ

1) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የውጭ ሚሲዮኖች ውስጥ በቋሚነት ተቀጥረው ወይም ተመድበው የሚያገለግሉ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች በዚህ መመሪያ አንቀፅ /6/ ንዑስ አንቀፅ /1/ ስር ከተመለከቱት መስፈርቶች በተጨማሪ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የምዝገባ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

   ሀ) የጸና የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ፤ እና

   ለ) ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፡፡

2) ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ተፈላጊ ማስረጃዎች ተሟልተው ሲቀርቡ በርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የዲያስፖራና ህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት በኩል ተላልፈው ምዝገባው በክልሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ አማካይነት ይፈፀማል፡፡

# ክፍል ሦስት

## ስለ ዝግ የባንክ ሂሳብ አከፋፈት፣ ስለመኖሪያ ቤቶች አይነትና የግንባታ ወጭ

### 9. ስለ ዝግ ሂሳብ አከፋፈት

1) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዚህ መመሪያ መሠረት በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ለተደራጁም ሆኖ በግል ለተመዘገቡ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዩጲያዊያንና ትውልደ-ኢትዩጲያዊያን ዝግ የባንክ ሂሣብ የመክፈት አገልግሎት ይሰጣል፤

2) ሁሉም ማኀበራት የተጠቀሰውን የጋራ ሂሣብ ካስከፈቱ በኃላ በእያንዳንዳቸው ስም ሰብሲዲያሪ ሌዠር ተይዞላቸው ከምዝገባ በፊት በመመሪያው የተወሰነውን የቅድሚያ ክፍያ ወደዚሁ ሂሣብ ገቢ እንዲሆን ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

3) ባንኩ ገቢ የተደረገውን የእያንዳንዱን ማኀበር የገንዘብ መጠን በተመለከተ ለክልሉ ህብረት ስራ ማኀበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲም ሆነ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማረጋገጫ ይልካል፤

4) በክልሉ ውስጥ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ የዲያስፖራ አባላት እንዲገነባላቸው የሚፈልጉትን ቤት ግንባታ ገንዘብ የሚከፍሉት በውጭ ምንዛሪ ይሆናል፤

5) የግል ተመዝጋቢዎች ክፍያውን የሚፈጽሙት ሃገራቱ በምትገበያይባቸው ገንዘቦች ብቻ ይሆናል፤

6) ተመዝጋቢዎች ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በስማቸው የተከፈተ የዲያስፖራ ሂሣብ ያላቸው እንደሆነ ገንዘቡ ከዚህ ሂሳብ ወደተደራጁበት የመኖሪያ ቤት ኀብረት ሥራ ማኀበር ሂሳብ እንዲዞርላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፤

7) ነባር ማኀበራት ሆነው በሌላ ባንክ በኩል ዝግ ሂሳብ አስከፍተው የቆዩ መሆናቸው ከታወቀ ይህንኑ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማዞር አዲስ ሂሳብ መክፈት ይጠበቅባቸዋል፤

8) በግል ተመዝጋቢዎችና በማህበር የተደራጁ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊ ኢትዩጲያውያንና ትውልደ-ኢትዩጲያውያን ምዝገባውንም ሆነ ዝግ የባንክ ሂሣብ የማስከፈቱን ሂደት ለማስፈፀም ከዚህ በታች የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልተው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡-

ሀ) የጸና የፓስፖርትና ከሚኖርበት አገር የተሰጠ የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ወረቀት ቅጂዎች፤

ለ) የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው እንደሆነ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ወረቀት ቅጂ ፤

ሐ) የፓስፖርት መጠን ያላቸው ሁለት ፎቶ ግራፎች ፤

መ) ከተመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት ጠቅላላ የግንባታ ወጪ ውስጥ 50 ከመቶ የሚሆነው በውጭ ምንዛሪ ተልኮ በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ ገቢ ስለመደረጉ የሚያሳይ የክፍያ ደረሰኝ ቅጅ፡፡

9) በተለያዩ የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና ሌሎች የሙያ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩና በአገር ውስጥ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ እየኖሩ ያሉ ተመላሽ የዲያስፖራ አባላት የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ክፍያውን በኢትዮጵያ ብር ፈፅመው ዝግ የባንክ ሂሣብ ሊያስከፍቱ ይችላሉ፡-

ሀ) በዜግነት ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ተመላሽ የዲያስፖራ አባላትን በተመለከተ ከዋናው ጋር የተገናዘበ የጸና የኢትዩጲያ ፓስፖርት ቅጂ፤

ለ) የሌላ አገር ዜግነት ያላቸውን ትውልደ-ኢትዩጲያውያን በተመለከተ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ወረቀት ቅጂ፤

ሐ) ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በአገር ውስጥ መቆየታቸውን የሚያሳይና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሠጠ ማስረጃ፤

መ) በአለም አቀፍና በአህጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑና በግል ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነ ወርሀዊ ክፍያቸው በኢትዮጵያ ብር የሚፈፀም ግብር ከፋዮች ስለመሆናቸው የሚያሣይና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ ማስረጃ፤

ሠ) መተዳደሪያቸው ሌላ አይነት ገቢ ከሆነ በተመሣሣይ ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ቅጂ ፡፡

10) በተለያዩ የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና ሌሎች የሙያ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ሆነው ከሁለት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ በሀገር ውስጥ እየኖሩ ያሉ ኢትዮጵያዊና ትውልደ-ኢትዩጲያዊ ተመላሽ የዲያስፖራ አባላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /9/ ሥር የተገለጹትን መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ ተፈላጊውን ክፍያ በውጭ ምንዛሪ በመፈፀምና ዝግ ሂሣባቸውን በኢትዩጲያ ብር በማስከፈት የዚህ መመሪያ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

10. **ስለመኖሪያ ቤቶች ዓይነት፣ ስፋት እና የግንባታ ወጭ**

1) በግል እየተመዘገቡም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት እየተደራጁ የውጭ ሀገር ነዋሪ ኢትዩጲያዉያንና የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ-ኢትዩጲያውያን በክልሉ ከፍተኛና መካከለኛ ከተሞች ውስጥ የሚገነቧቸው መኖሪያ ቤቶች አፓርትመንትና ታውን ሀውስ ሆነው የተገኙ እንደሆነ የቤቶቹ ስፋትና ጠቅላላ የግንባታ ወጭ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) የተመረጠው አፓርትመንት (G+4 እና ከዚያ በላይ) ሲሆን፡-

i. ቤቱ ባለ 2 መኝታና የቦታው ስፋት 74 ካ.ሜ. የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው ብር 424,390/ አራት መቶ ሀያ አራት ሽህ ሶስት መቶ ዘጠና ብር/ ይሆናል፤

ii. ቤቱ ባለ 3 መኝታና የቦታው ስፋት 100 ካ.ሜ. የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው 573,500 /አምስት መቶ ሠባ ሶስት ሽህ አምስት መቶ ብር/ ይሆናል ፤

iii. ቤቱ ባለ 4 መኝታና የቦታው ስፋት 136 ካ.ሜ. የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው ብር 779,960 / ሠባት መቶ ሠባ ዘጠኝ ሽህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ብር/ ይሆናል፡፡

ለ) የተመረጠው ታውን ሀውስ (G+2) ሲሆን፡-

i. ቤቱ ባለ 3 መኝታና የቦታው ስፋት 114 ካ.ሜ. የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው ብር 693,120/ ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ሽህ አንድ መቶ ሀያ ብር/ ይሆናል፤

II. ቤቱ ባለ 4 መኝታና የቦታው ስፋት 150 ካ.ሜ. የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው ብር 912,000 / ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሽህ ብር / ይሆናል፡፡

2) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ ስር የተመለከቱት ወጭዎች ይህ መመሪያ በስራ ላይ በዋለበት ወቅት የሚታየውን የገበያ ዋጋ የሚገልፁ ሲሆኑ እንደየከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታና ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ዕድገት በጥናት ላይ የተመሰረተ ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይችላል፡፡

11. **በጋራ ስለሚገነቡ ከፍተኛ ህንፃዎች**

በጠቅላላው ከ56 ያላነሱ አባላትን በማቀፍ የተደራጁ አራትና ከዚያ በላይ የሆኑ የዲያስፖራ መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት በመሃል ከተማ ከፍተኛ ህንፃዎችን መገንባት ከፈለጉና ይህንኑ አግባብ ያለው የከተማ አስተዳደር ከተቀበለው ለዚሁ

ፕሮጀክት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲገነቡ ሊፈቅድላቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ይሆናል፡-

**የህንጻ ከፍታ፣ የአባላት ብዛት እና የቤት አይነት መግለጫ**

1. **በክልሉ በሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች/ከፍተኛና መካከለኛ ከተሞች/ አፓርትመንት ለመገንባት (G+4 እና በላይ) አማራጭ የቤት ዓይነት ስብጥር እና የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት (ነባርም ይሁን አዲስ አባላት)**

| አማራጭ | የአባላት ብዛት | የቤት አይነት | በአንድ አፓርትመንት የሚኖር የቤቶች ብዛት ስብጥር | የሚያስፈልግ አማካኝ የቦታ ስፋት በሜ/ካ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ለአንድ ቤት | ጠቅላላ |
| 1 | 14 (1ማህበር) | ባለ2 መኝታ ቤት | 4 | 80 | 320 |
| | | ባለ3 መኝታ ቤት | 6 | 88 | 528 |
| | | ባለ4 መኝታ ቤት | 4 | 96 | 384 |
| | | ለአንድ አፓርትመንት ጠቅላላ የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት | | | 1232 |
| 2 | 14 (1ማህበር) | ባለ3 መኝታ ቤት | 7 | 88 | 616 |
| | | ባለ4 መኝታ ቤት | 7 | 96 | 672 |
| | | ለአንድ አፓርትመንት ጠቅላላ የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት | | | 1288 |
| 3 | 14 (1ማህበር) | ባለ3 መኝታ ቤት | 8 | 88 | 704 |
| | | ባለ4 መኝታ ቤት | 6 | 96 | 576 |
| | | ለአንድ አፓርትመንት ጠቅላላ የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት | | | 1280 |

የግርጌ ማስታወሻ፡- 1. በግል የሚመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች 14 በመሆን የሚኖሩበትን አገር መነሻ

በማድረግ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

2. ከላይ የተመለከተው የቦታ ስፋት ከተማው ባዘጋጀው የአካባቢ ልማት ፕላን ላይ ተመስርቶ የቦታ ስፋቱ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡

I. በክልሉ በሚገኙ ከከፍተኛና መካከለኛ ከተሞች ውጭ በታውን ሃውስ (G+1) ቤት ለመገንባት የሚያስፈልግ የቤት አይነት፣ የአባላት ብዛትና የቦታ ስፋት

| አማራጭ | የቤት አይነት | የአንድ ማህበር የሚይዘው አባላት ብዛት | ለአንድ ቤት የሚሰጠው የቦታ ስፋት በካ/ሜ | የሚያስፈልግ አማካይ የቦታ ስፋት በሜ/ካ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባለ2 መኝታ ቤት | 14 | 120 | 1680 |
| 2 | ባለ3 መኝታ ቤት | 14 | 135 | 1890 |
| 3 | ባለ4 መኝታ ቤት | 14 | 150 | 2100 |

የግርጌ ማስታወሻ፡- የማህበር አባላት ከላይ ከተመለከተው የመኝታ ቤት ምጣኔ በተለየ መንገድ መደራጀት ከፈለጉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የሚመርጡትን የቤት አይነት ዲዛይን ራሳቸው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ባለ ድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 12. የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ

በሌላ ህግ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ የዚህን መመሪያ ተፈፃሚነት በተመለከተ የሚከተሉት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የተደራጁ ወይም በግል የተመዘገቡ የቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊ ኢትዮጲያውያንና ትውልደ-ኢትዮጲያውያን ዲያስፖራዎችን አስመልክቶ ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ አሰራር እንዲከተሉ የሚያግዝ ማንዋል ያዘጋጃል፣ ስለተፈፃሚነቱም የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

2) ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር ለግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ግንባታ የሚውል መሬትና የመሰረተ ልማት አውታሮች ተዘጋጅተው መቅረባቸውን ይከታተላል፣ በራሣቸው፣ በማህበራቱም ሆነ በሚመለከታቸው የከተማ አስተዳደሮች ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን ዲዛይኖች በህንጻ ሹም አማካኝነት የማጸደቅና ሌሎች ድጋፎችን ይሰጣል፤

3) በተለያዩ ደረጃዎች ላይ በሚገኙ ከተሞች ዘንድ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሞዴል የግንባታ ዲዛይኖችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፣ ራሣቸው ከተሞቹ ያዘጋጁ ዘንድ ተፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

4) ቤቶች ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የሚኖረውን የግንባታ ሂደት በየከተሞቹ ስር የተደራጁት የህንጻ ሹም ጽ/ቤቶች እንዲከታተሏቸው ያደርጋል፡፡

## 13. የክልሉ ህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ

በሌላ ህግ የተሠጠው ስልጣን እንደጠተበቀ ሆኖ የክልሉ ህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ የዚህን መመሪያ ተፈፃሚነት በተመለከተ የሚከተሉት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ-ኢትዮጵያውያንና ተመላሽ ዲያስፖራዎች በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ለምዝገባ የሚያስፈልጓቸውን የአደረጃጀት ፎርማቶችና ሌሎች ቅፃቅጾች ያዘጋጃል፣ ወይም በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አማካኝነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደ አስፈላጊነቱ ውክልና ሰጥቶ እንዲደራጁ ያደርጋል፤

2) በውጭ የሚኖሩ ኢትዩጲያውያንና ትውልደ-ኢትዩጲያውያን በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ለመደራጀት የሚያስፈልጋቸው ዝርዝር መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲደርሣቸው ያደርጋል ፤

3) ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው በምዝገባው ለመጠቀም የወሰኑና አስቀድመው በውጭ አገር የተደራጁ ወገኖች ካሉ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከኢትዩጲያ ንግድ ባንክ ጋር በመተባበር የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ብሎም ከቤቱ አጠቃላይ የግንባታ ወጭ ውስጥ 50 ከመቶውን ከከፈሉና ሌሎች ተዛማጅ መስፈርቶችን አሟልተው ከተገኙ ይህንኑ በማረጋገጥ የምዝገባ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

4) በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት በኩል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚላክለት የአባላት ዝርዝርና ከኢትዩጲያ ንግድ ባንክ በሚያገኘው መረጃ መሰረት ተፈላጊውን ክፍያ ያጠናቀቁ ማህበራት በመረጡት ከተማ መኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስችላቸውን ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

5) በዚህ መመሪያ መሠረት የተመዘገቡና ሌሎች ተፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎችን ያሟሉ ማህበራት የቦታ ዝግጅትና የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶችን ባፋጣኝ ያገኙ ዘንድ ዝርዝራቸውን አግባብ ላለው የከተማ አስተዳደርና በተለይም ለህንጻ ሹም ጽ/ቤት ያስተላልፋል፤

6) ነዋሪነታቸው በውጭ ቢሆንም በምዝገባው ወቅት አገር ቤት የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላት በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ከከፈቱ በኃላ በአካል ቀርበው እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤

7) በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚያገለግሉ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች ዝርዝር በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት በኩል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚላክለትና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚያገኘው መረጃ መሠረት በአባልነት የታቀፉባቸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የግንባታውን ወጪ 50 ከመቶ ከፍለው ያጠናቀቁ መሆናቸው ከተረጋገጠ የምዝገባ እውቅና ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

8) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ-ኢትዮጵያዊያን ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች ምዝገባ የፈጸሙባቸውን ቅጾች፣ የመተዳደሪያ ደንቦች፣ የአመራር ምርጫ ቃለ-ጉባኤዎችና ሌሎች ሰነዶች በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አማካኝነት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይረከባል፣ ያደራጃል፤

9) የተፈላጊ ቤቶች ግንባታ በውላቸው መሠረት እንደተጠናቀቀ ቤቶቹን በየመተዳደሪያ ደንቦቻቸው መሠረት ለየማህበር አባላቱ ያስረክባል፤

10) ቤቶቹ ተገንብተው እስኪጠናቀቁ ድረስ የግንባታ ሂደቱ በትጋት የሚከታተል ራሱን የቻለ የውስጥ አደረጃጀት ይፈጥራል፡፡

## 14. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የዲያስፖራና የህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክቶሬቱ የዚህን መመሪያ አተገባበር አስመልክቶ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) ጉዳዩን በሚመለከት የክልሉ መንግስት አካላት በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማንዋሎች በወቅቱ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይልካል፤

2) በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ መኖሪያ ቤት ለመስራት ጥያቄ ያቀረቡትን ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ዝርዝር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመቀበልና በየሚመርጡት ከተማ ለይቶ በማደራጀት ጉዳያቸውን ለክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ለህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤

3) በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ከኢፌዴሪ ሚሲዮኖች በኩል ወደ ክልሉ የሚላኩትን የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት መመስረቻ ቃለ-ጉባኤዎች፣ መተዳደሪያ ደንቦችና ሌሎች በአባላት የተሞሉ ቅፃቅጾች ለክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ለህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

4) በኤጀንሲው በኩል ማህበራቱ የተመዘገቡባቸውን የዕውቅና ማረጋገጫ ደብዳቤዎች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት አባላቱ ለታቀፉባቸው የኢፌዴሪ ሚሲዮኖች እንዲደርሷቸው ያስተላልፋል፡፡

## 15. የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ/የቤቶች ልማት ድርጅት

እንደነገሩ ሁኔታ ኤጀንሲው ወይም ድርጅቱ የዚህን መመሪያ አተገባበር በሚመለከት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) ለግንባታ ስራው የተመረጠ እንደሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት ከተደራጁትና ስለዚሁ እውቅና ከተሰጣቸው አባላት ጋር የግንባታ ውል ስምምነቶችን ይፈራረማል፤

2) የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በተረከቡት መሬት ላይ የሥራ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን በማሰማራትና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የቤቶቹን ግንባታ በውሉና በዲዛይኑ መሠረት ያከናውናል፤

3) ግንባታውን ለማስጀመር የሚያስፈልገውና በዝግ የባንክ ሂሣብ የተቀመጠው የማህበራቱ ገንዘብ እንዲሁም ሥራውን በየደረጃው ለማከናወንና ለማጠናቀቅ የሚያስችለው ተጨማሪ ፋይናንስ በየጊዜው በሚያቀርበው የግንባታ አፈጻጸም ሪፖርት መሠረት እንዲለቀቅለት ይጠይቃል፤

4) የቤቶቹን ስራ በየደረጃው ካከናወነ በኃላ ግንባታቸው የተጠናቀቀውን መኖሪያ ቤቶች አግባብ ላለው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ክፍልያስረክባል፡፡

## 16. አግባብ ያለው የከተማ አስተዳደር

1) አግባብ ያለው የከተማ አስተዳደር የዚህን መመሪያ አተገባበር በተመለከተ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ መሠረት ተደራጅተው የምዝገባ ሰርተፊኬት ለተሰጣቸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የቤት መስሪያ ቦታና የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ ስለዚሁ አገልግሎት መሰጠት ለአደራጅ መስሪያ ቤቱ ያሳውቃል፤

ለ)ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ለግንባታው የሚያሥፈልጉት የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሟሉ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ሐ) እንደየከተሞቹ ባህሪ እና እንደየማህበራቱ ምርጫ ዲዛይን እንዲዘጋጅ ድጋፍ ይሰጣል፣ የሚገነቡ መኖሪያ ቤቶችን ስታንዳርድ ዲዛይን ያዘጋጃል፣ ማህበራቱ ራሣቸው ሲያቀርቡም ይህንኑ ተቀብሎ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

2) የከተማ አስተዳደሩ ለነባርም ይሁን ላዳዲስ ማህበራት በዚህ መመሪያ መሠረት የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሚሰጠው በምደባ ስርአት ሆኖ በሊዝ መነሻ ዋጋ ይሆናል፡፡

## 17. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዚህን መመሪያ አተገባበር በተመለከተ በልዩ ልዩ አካላቱ በኩል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) **የውጭ ሚሲዮኖች ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በግል ለተመዘገቡና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ለተደራጁ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ማስፈጸሚያ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ በየሚሲዮኖቹ እንዲሁም በየተወከሉባቸው አገሮች ውስጥ ለሚገኙ ኢትዮጲያውያንና ትውልደ-ኢትዮጲያውያን ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎችን ያከናውናሉ፤

ለ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም መመሪያው ላይ የተቀመጡትን የምዝገባ ቀናት፣ የምዝገባ ቦታና ተመዝጋቢዎች የሚጠበቁባቸውን መስፈርቶች በግልጽ ያስገነዝባሉ፣ አደረጃጀቶቻቸው በአግባቡ እንዲጠናቀቁ ያደርጋሉ፤

ሐ) በግልና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች አማካኝነት እንዲሞሉ ከሚኒስቴሩ የሚላኩ ቅጾችን በበቂ መጠን በማባዛት ያስሞላሉ፤

መ) በግልም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም የተመዘገቡትን አባላት ዝርዝር እንዲሁም ሌሎች የተሞሉ ቅጾችንና ተፈላጊ መረጃዎችን በጥንቃቄ በማደራጀት በዲፕሎማቲክ ፓውች አካተው ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋሉ፤

ሠ) ስለ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር በክልሉ ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚላኩት የተለያዩ ሰነዶች፣ ቅጾችና ውሎች በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን ያረጋግጣሉ፤

ረ) ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች ወይም ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ሌሎች ጉዳዮች ያጋጠሙ እንደሆነ ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በወቅቱ ያቀርባሉ፤

ሰ) የግል ተመዝጋቢዎችን በተመለከተ የግድ መደራጀት ባይጠበቅባቸውም ለአፈጻጸም አመች ይሆን ዘንድ በቡድን እየለዩ ዝርዝራቸውን ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ከሸኝ ደብዳቤ ጋር ይልካሉ፤

ሸ) የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በዚህ መመሪያ መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣሉ፤

ቀ) በክልሉ ከተሞች ውስጥ የሚደራጅ የማናቸውም አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላት ቁጥር 14 እና ከዚያ በላይ መሆኑን በማረጋገጥ የሚቀርቡላቸውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦች ተጠቅመው በቃለ-ጉባዔ የተደገፈ የአመራር አባላት ምርጫ እንዲከናወን ያደርጋሉ፤

በ. በያንዳንዱ አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የተሞሉትን የአባላት ቅጾች፣ የተደራጁባቸውን መተዳደሪያ ደንቦች፣ የአመራር አባላቱን

የመረጡባቸውን ቃለ ጉባኤዎችና የሚፈልጉትን የመኖሪያ ቤት አይነት ከሸኝ ደብዳቤ ጋር ለዳይሬክቶሬት ጄኔራሉ ያስተላልፋሉ፡፡

2) **የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) ለአገልግሎት አሰጣጡ የሚያስፈልጉት መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ቅፃቅጾች በወቅቱ ለሚሲዮኖች እንዲደርሱ ያደርጋል፤

ለ) ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚያገኛቸውን ምላሾች በወቅቱ ለሚሲዩኖች ያስተላልፋል፤

ሐ) ከሚሲዮኖች በኩል የሚተላለፉለትን የተሞሉ ቅጾች፣ የማህበራት መመስረቻ ቃለ ጉባዔዎች፣ መተዳደሪያ ደንቦችና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ለክልሉ ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ይልካል፣ ክትትል ያደርጋል፤

መ) የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባ ዕውቅናን የሚገልጽ ደብዳቤ ተፅፎ ከዚሁ ኤጀንሲ በኩል ሲደርሰው ይህንኑ ለሚሲዮኖች ያስተላልፋል፤

ሠ) ከውጭ ሚሲዮኖች፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ከክልሉ ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ/ድርጅት እና ከህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ጋር የሚደረጉትን የስራ ግንኙነቶች ይከታተላል፣ አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል፤

ረ) ከየሚሲዮኑ በሚደርሰው የግል ተመዝጋቢዎች ዝርዝር መሠረት በእያንዳንዱ ማኅበር ስም እየተመዘገበ በጥል አካውንት አይነት የባንክ ሂሣብ እንዲከፈት ያደርጋል፤

ሰ) የግል ተመዝጋቢዎችን በማኅበር እያደራጀ ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለክልሉ ህብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤

ሸ) ወደ አገር ቤት ተመላሽ ዲያስፖራዎችን በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሥፈርቶች መሟላታቸውን እያረጋገጠ የምዝገባ ብቁነት ማስረጃ ይሰጣል፡-

I. የተመላሽ ዲያስፖራው የጸና የፖስፖርት ቅጂ፤
II. ተመላሽ ዲያስፖራው የሌላ አገር ዜግነት የወሰደ ከሆነ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ወረቀት ቅጂ፤
III. ባለትዳር የሆነ እንደሆነ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ቅጅ/ከዋናው ጋር የተገናዘበ/
IV. በቅርብ ጊዜ የተነሣቸውና ሁለት የፖስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎች፤

V. ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የምዝገባ ቅጽ ሞልቶና የውል ሰነድ ፈርሞ ማቅረብ፤

VI. በመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታው ወጪ 50 ከመቶ በውጭ ምንዛሪ ተከፍሎ በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ ገቢ ስለመደረጉ የሚያስረዳና ከዋናው ጋር የተገናዘበ የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማሳየት፡፡

## 3) የሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው በማገልገል ላይ የሚገኙ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅው በመሙላት የሚልኩለትን የምዝገባ ቅጾች፣ መተዳደሪያ ደንቦች፣ የአመራር አባላቱን የመረጡባቸውን ቃለ-ጉባኤዎችና የፈለጉትን የመኖሪያ ቤት ዓይነት ከየሚሲዮኖቹ ሽኝ ደብዳቤ ጋር ለክልሉ ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤

ለ) የዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች የምዝገባ መርሀ-ግብር በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ መደረጉን በቅርብ ይከታተላል፣ ተፈላጊው መረጃ በሚሲዮኖች አማካኝነት እንዲደርስ ያደርጋል፤

ሐ) በስማቸው የባንክ ሂሣብ የሚከፈትላቸውን ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች ዝርዝር ለባንኩ ያስተላልፋል፡፡

## 18. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

የኢትዩጲያ ንግድ ባንክ የዚህን መመሪያ አተገባበር በተመለከተ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) በግልም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ለሚቀርቡና በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዩጲያውያንና ትውልደ-ኢትዩጲያውያን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊዎች እንደ አግባብነቱ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከክልሉ ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ በሚደርሰው ዝርዝር መሠረት የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤

2) በማህበራቱ ስም የተከፈተው ሂሳብ በየመተዳደሪያ ደንቦቻቸውና በውሉ መሰረት እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤

3) በግል ተመዝጋቢዎች የሚከፈትን የባንክ ሂሳብ በተመለከተ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰጣል፤

4) ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ለግል ተመዝጋቢዎች ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል የጥል ሂሣብ ይከፍታል፤

5) በተመሳሳይ ሁኔታ ከክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተደራጁ ወገኖች ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል ሂሣብ ይከፍታል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 19. ስለውክልና

1) በውጭ አገር የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ-ኢትዮጵያዊ በመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊነት በዚህ መመሪያ መሠረት ለመመዝገብና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ለመከታተል በአካል መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ይህንኑ በአገር ቤት የሚፈፅምለት ሰው በህግ አግባብ ሊወክል ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ ተወካይ ከአንድ በላይ ለሆኑ ዲያስፖራዎች በአንድና በተመሣሣይ ጊዜ ወኪል ሊሆን አይችልም፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የተወከለ ማንኛውም ሰው የማህበር አባልም ይሁን በግል የተመዘገበን ዲያስፖራ ወክሎ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ውስጥ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች አክብሮ የመስራት ኃላፊነት አለበት፤

3) ተወካዩ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማቅረብ ወካዩ አላግባብ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ እንዳልተገባ ጥቅም ተጋሪ ተቆጥሮ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 20. ስለምዝገባ ጊዜ

የግል ተመዝጋቢዎችም ሆኑ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ አባላት ምዝገባ በክልሉ ከተሞች ውስጥ ይህ መመሪያ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል ፡፡

### 21. ስለ ሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር

1) ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ይሆን ዘንድ በዝግ ሂሳብ የተቀመጠ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ገንዘብ የክልሉ ህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና

ማስፋፊያ ኤጀንሲ ሓላፊ ሲፈቅድና ስለዚሁ ጉዳይ ለባንኩ ደብዳቤ ሲጽፍ ብቻ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፤

2) የግል ተመዝጋቢዎች የሚከፈትላቸው የግል ሂሣብ ወደተደራጁበት ማኅበር ሂሳብ እንዲዛወር ከኤጀንሲው ትዕዛዝ የደረሰው እንደሆነ ባንኩ ይህንኑ ፈፅሞ ትዕዛዙን ለሰጠው ክፍል ያሣውቃል፡

## 22. ስለ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ክትትል

1) በግል ተመዝግበው ወይም በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው የቀረቡ የዲያስፖራ አባላት ቤቶች ግንባታ የሚካሄደው በክልሉ ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ፣ በቤቶች ልማት ድርጅት ወይም ማህበራቱ በመረጡት በዘርፉ ፈቃድ የተሰጠው ሌላ ማናቸውም የስራ ተቋራጭ አማካኝነት ሊሆን ይችላል፤

2) ግንባታው የሚከናወነው በክልሉ የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ ወይም በቤቶች ልማት ድርጅት አማካኝነት የሆነ እንደሆነ እነዚሁ ተቋማት የግንባታውን ሂደት፣ የክፍያውን አለቃቀቅ እና የጥራቱን ቁጥጥር ለማስፈፀም የሚያግዙ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋሉ፤

3) በማህበር የሚገነቡ መኖሪያ ቤቶች ርክክብ የሚፈፀመው ግንባታቸው መቶ በመቶ መጠናቀቁ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

## 23. ስለ መኖሪያ ቤት ርክክብና ቅደም ተከተል አወሳሰን

1) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በማህበር ተደራጅተው የነበሩና በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ-ኢትዮጵያዊያን በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልተው ከተመዘገቡ ከአዲስ ተመዝጋቢ ማህበራት ጋር የድሉ ተጠቃሚዎች ለመሆን ይችሉ ዘንድ በእጣ እንዲለዩ ይደረጋል ፤

2) በማህበር ተደራጅተው ቤት ያስገነቡ አባላት የመኖሪያ ቤት ርክክብ ማህበራቱ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል ጋር ባደረጉት የውል ስምምነት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሆኖም የያንዳንዱ ማህበርተኛ ቤት ርክክብ የሚፈጸመው በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ነው፤

3) በግል የተመዘገቡትን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊዎች በተመለከተ የቤት ግንባታው የሚካሄድላቸው በጋራ ሲሆን ክፍፍሉ የመረጡትን ቤት መሠረት በማድረግ በዕጣ እንዲፈፀም ይደረጋል፤

4) የመጀመሪያውን ፎርማሊቲ አሟልተው 50 ከመቶ ክፍያ ያጠናቀቁና እውቅና ያገኙ ማህበራት ቁጥር ለግንባታ ከተዘጋጀው መሬት በላይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የቦታ እደላው የየማህበራቱ ተወካዮች በተገኙበት በዕጣ ይከናወናል፤

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት መሬት በዕጣ የደረሳቸው ማነበራት ያገኙት መሬት በተለያዩ የከተማው አካባቢዎች ተበታትኖ የሚገኝ ከሆነ ድርሻቸውን ማደላደል የሚቻለው በዕጣ ይሆናል፡፡

## 24. ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ

1) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን መስፈርቶች ሳያሟላ ተመዝግቦ የተገኘ ማንኛውም የግል ወይም የማህበር ተጠቃሚ ከምዝገባ ፕሮግራሙ ከመሰረዙ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተደነገገው ቢኖርም ከማህበሩ አባላት መካከል መስፈርቱን ሣያሟላ ወይም ሣያሟሉ ተመዝግቦ ወይም ተመዝግበው የተገኘው/ የተገኙት አንዱ ወይም የተወሰኑት አባላት መስፈርቶችን የማያሟሉ ሲሆኑ እነርሱ ብቻ በግል ተጠያቂ ሆነው የማህበሩ ህልውና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## 25. ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ

በመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊነት ከተመዘገቡት የግልም ሆነ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ምዝገባ ተሰርዞ ገንዘቡ እንዲመለስ የተወሰነበት ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ማህበር የሚመለስለት ገንዘብ በወቅቱ የኢትዮጵያ ብር ምንዛሪ የሚሰላ ሆኖ በቁጠባ ውሉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚያገኘውን የወለድ ጥቅም በመጨመር ይሆናል፡፡

## 26. ክልከላ

1) ክልሉ በሚሰራበት የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት ክልከላዎች በሙሉ በዚህ የማስፈጸሚያ መመሪያ ለተሸፈኑት ተጠቃሚዎችም በተመሣሣይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

2) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውጭ በሆነ አሰራር በመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፈላጊነት መመዝግብም ሆነ እንዲመዘገቡ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

27. **ስለቅጣት**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡትን የምዝገባ መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ ወይም ክልከላዎችን ተላልፎ ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ ተመዝግቦ የተገኘ ማንኛውም ተመዝጋቢም ሆነ ተወካዩ አግባብ ባለው የወንጀልና የፍትሐብሔር ሕጐች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

28. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ እየታየ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሊሻሻል ይችላል፡፡

29. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

ባህር ዳር

መስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም

የአማራ ብሄራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት

**ቅጽ 001**

| |
|---|
| **ፎቶ** |

<u>አባሪ አንድ</u>

**በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በአፓርትመንት ወይም ታውን ሀውስ በግል የመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ለመመዝገብ የቤት ፍላጎት መግለጫ ቅጽ**

1. **የአመልካች ሁኔታ፣**

   1.1. ስም የአባት ስምየአያት ስም ---------------------- ፆታ ---------------- ዕድሜ-------------------ብሔር---------------------------ዜግነት------------- የፓስፖርት ቁጥር--------------------------------

   1.2 የአመልካች እናት ስም ------------------------- የእናት አባት ስም ----------------- የእናት አያት ስም -------------------------------------

   1.3 የመኖሪያ አድራሻ

   - አገር---------------------ከተማ------------------------------------
   - ፖ.ሳ.ቁ.--------------------------------- ፋክስ ቁጥር----------------
   - ስልክ ቁጥር-------------------------------ኢሜል ------------------

   1.4 የትዳር ሁኔታ

   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐

   1.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም----------------የአባት ስም----------------- የአያት ስም --------------------

2. **የሚፈልጉት የቤት አይነት**

   2.1. አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ)ከሆነ ፤

   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

   2.2 ታውን ሀውስ ከሆነ፡

   ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

3. የገቢ ሁኔታ

3.1. የአመልካች ወርሃዊ የገቢ መጠን በብር ----------------------- ምንጭ --------------
3.2. የትዳር ጓደኛ የገቢ መጠን በብር ------------------------ ምንጭ -----------------
3.3. ጠቅላላ የገቢ መጠን በአኃዝ ------------ /በፊደል--------------------------------

4. የተወካይ መረጃ፤

4.1የተወካዩ ስም ከነአያት--------------------------------------------------------

4.2. የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-

- ክልል---------------------------ከተማ--------------------------------
- ዞን/ክ/ከተማ------------------------------ወረዳ ----------------------
- ቀበሌ ---------------------------የቤት ቁጥር --------------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር -------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር -------------

5. ለምዝገባ የሚያስፈልግ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ

5.1 በቅድሚያ በልዩ ዝግ ሂሳብ ያስቀመጠው ዝቅተኛ መጠን ብር በአኃዝ ------------------ /በፊደል------------------------------------------------------------------------------------------/

5.2 የዝግ ሂሳብ የቁጠባ ደብተር ቁጥር ------------------------------------ ቅርንጫፍ ----------------------

6. ሂሳብ የሚከፍትበትና የቤቱን ዋጋ ክፍያ የሚፈጸምበት አማራጭ መንገድ፡-

6.1. የክፍያ አፈጻጸም በአንድ ጊዜ (100%) ☐ በሁለት ጊዜ (50%) ☐

7. እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

7.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፣

7.2 ግንባታ እንዲካሄድልኝ በመረጥኩት ከተማ ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በመንግስት በተዘረጉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

7.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ማስቀመጤን፣ ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ሲሠጥ የማስቀምጥ መሆኑን፣

7.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

7.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረክብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

7.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

7.7 ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሙሉ ስም______________________________

ፊርማ___________________________

ቀን ____________________________

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ በግል ተመዝጋቢዎች ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው፡፡

ቅጽ 002

ፎቶ

<u>አባሪ ሁለት</u>

**በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ**

1. **የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ-----------------------------------------------------የመኖሪያቤት ኃ/የተ/የህ/ስ/ማ**
2. **የአመልካች ሁኔታ፤**
   2.1. ስም --------------- የአባት ስም ----------------የአያት ስም ------------------ፆታ --------ዕድሜ-----------ብሔር---------------ዜግነት----------- የፓስፖርት ቁጥር------------
   2.2 የአመልካች እናት ስም ----------------------- የእናት አባት ስም ------------------------------ የእናት አያት ስም-----------------------------------
   2.3. **የመኖሪያ አድራሻ**
   2.3.1 አገር-------------------------------------
   2.3.2 ከተማ-----------------------------------
   2.4 የትዳር ሁኔታ
   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐
   2.5. ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም ----------------የአባት ስም---------------የአያት ስም------------------
3. **የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት**
   3.1 አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ)ከሆነ፤
   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐
   3.2 ታውን ሀውስ ከሆነ፡
   ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐
4. **የተወካይ መረጃ፤**
   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት---------------------------------------------------
   4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-
   - ክልል--------------------------ከተማ-------------------------------

- ዞን/ክ/ከተማ------------------------------ወረዳ ----------------------
- ቀበሌ --------------------------የቤት ቁጥር --------------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር ------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር -------------

5 **እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች**

5.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉትበማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኑን፤

5.2 ግንባታ እንዲካሄድልኝ በመረጥኩት ከተማ ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በቤት ልማት ፕሮግራም ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፤

5.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥኩ መሆኑን እና ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ሲሰጥ የማስቀምጥ መሆኔን፤

5.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፤

5.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፤

5.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም፤

5.7 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያማላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም________________________________

ፊርማ ____________________________

ቀን ____________________________

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ የህ/ስ/ማህበሩ አባል ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው